17ኛ ዓመት ቁጥር 1
17th Year No 1

ባህር ዳር ህዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም
Bahir Dar 5th, December 2011

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG
# OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር **14.60** **Price Birr** | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312<br>P.O.Box 312 |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| **ደንብ ቁጥር 88/2004 ዓ.ም**<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን አጠቃቀም መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | **Regulation No. 88/2011**<br>The Amhara National Regional State The Use of Sales Register Machine Determination, Council of Regional Government Regulation. |

| ደንብ ቁጥር 88/2004 ዓ.ም | Regulation No. 88/2011 |
|---|---|
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ስለመጠቀም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE USE OF SALES REGISTER MACHINE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE |

በተሻለ መረጃ ላይ የተመረኮዘ የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መከተል ፍትሃዊና ትክክለኛ ግብር ለመጣልና ለመሰብሰብ የሚያስችልና ይኸዉ ተጠቃሚዉን ጭምር እንደሚያገለግል ስለታመነበት፣

ግብር ከፋዮች ተገቢ የሆነ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙና የክልሉ መንግስትም መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በአግባቡ እንዲሰበስብ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና ይህንኑ በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

ኋላቀር የነበረውን የገቢ ግብር አሰባሰብ ማሻሻል ለግብር ከፋዮችም ሆነ ለክልሉ መንግስት ጠቃሚ መሆኑን በመረዳት የክልሉ ምክር ቤት በተሻሻለው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 189/2003 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ሥለመጠቀም የደነገገውን ህግ በተሻለ መልኩ ማስፈፀም በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለዉ የብሄራዊ ክልሉ ህገመንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

WHEREAS, it is believed that following a revenue collection procedure depending on better information would enable to assess and collect fair and accurate tax as well as render service to the beneficiary thereof;

WHEREAS, it becomes imperative to put in place a system enabling taxpayers to maintain proper books of account and to appropriately collect the revenue that has to be collected by the Regional Government and legislate this by law;

WHEREAS, being cognizant of the fact that improving the backward collection of income tax is useful for the taxpayers and the regional government, it is necessary to execute, in a higher quality, the law enacted by the Regional Council on the use of sales register machine in the Ammended Income Tax Proclamation No. 189/2011;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, pursuant to the powers vested in it under the provision of Art. 58 Sub Art. /7/ of the Revised Regional Constitution, hereby issues this Regulation.

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ስለመጠቀም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/2004 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ"** ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ ነው፡፡

፪. **"የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ"** ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የሸቀጦችን ወይም የአገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሳሪያ ነው፡፡

፫. **"ደረሰኝ"** ማለት የጥሬ ገንዘብ ሽያጭ ደረሰኝ ሲሆን የዱቤ ሽያጭ ኢንቮይስንና ያለክፍያ የሚሰጥ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ማስተላለፊያ ደረሰኝን ይጨምራል፡፡

፬. **"በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራም"** ማለት በማይቀያየር ማስታወሻ ላይ የሚጫንና በትክክል ተለይቶ የተቀመጠን ስራ ለማደራጀት እንዲያገለግል የተዘጋጀ

# PART ONE
# GENERAL

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "the Use of Sales Register Machine, Council of Regional Government Regulation No. 88/2011".

## 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this regulation:-

1. **"Sales Register Machine"** shall mean a cash register machine or a point-of-sale machine;
2. **"Cash Register Machine"** shall mean a machine that uses a Firm Ware that is installed in an electronic programmable read only memory chip and can record the sale of goods or services, in lieu of the regular sales receipt;
3. **"Receipt"** shall mean cash sales receipt and include credit sales, invoices and receipts for the **transfer** of goods and services delivered or rendered free of charge;
4. **"Firm Ware"** shall mean a program which is burned on a Non-Volatile Memory and prepared for the purpose of organizing a work which is exactly defined and placed;

ፕሮግራም ነው፡፡

፭. **“የማይቀያየር ማስታወሻ”** ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ቢቋረጥም ተይዞ የቆየው መረጃ ተጠብቆ የሚቆይበት የኤሌክትሮኒክ ማስታወሻ ነው፡፡

፮. **“የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ”** ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያን የሚተካ ኮምፒውተራይዝድ የሆነ መሳሪያ ሲሆን የደንበኞችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈፃፀም ሂደትና የዴቢትና የክሬዲት ካርድ ሂሣብን የመመዝገብና የመከታተል፣ በክምችት ያለን ዕቃ የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሳሪያ ነው፡፡

፯. **“ታክስ”** ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የተርን ኦቨር ታክስ እና የገቢ ግብርን ያጠቃልላል፡፡

፰. **“ባለስልጣን”** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን ማለት ሲሆን እንደየሁኔታው በተዋረድ ያሉ የዞንና የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶችን ያጠቃልላል፡፡

፱. **“አቅራቢ”** ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ለታክስ ከፋዮች በሽያጭ የሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

፲. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፲፩. **“ፊሲካል ፕሪንተር”** ማለት የፊሲካል ማስታወሻ ያለው ሆኖ በስራ ላይ ያለውን

5. **“Non-Volatile Memory”** shall mean a type of electronic memory that retains data contents preserved therein evenif an electric power is turned off;

6. **“Point-of-Sale Machine”** shall mean a computerized machine that can replace the cash register machine having additional capability to record and track customers’ order, the process of its accomplishment, and debit and credit card accounts, in order to manage inventory of materials stored as well as enable to perform such other similar tasks;

7. **“Tax”** includes value added tax, turn over tax and income tax;

8. **“Authority”** shall mean the Amhara National Regional State Revenues Authority; provided, however, that it shall include the zonal and woreda’s or urban administration tax-collecting offices found hierarchically, as deemed necessary;

9. **“Supplier”** shall mean a person who supplies sales register machines to the taxpayers by sale;

10. **“Person”** shall mean a natural or a juridical person;

11. **“Fiscal printer”** shall mean a printer with a fiscal memory capable of serving with any

የውስጥ መገናኛ በመጠቀም ብቻ በማናቸውም የአሰራር ፕሮግራም ሊያገለግል የሚችል ፕሪንተር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችና ደረሰኝ አጠቃቀም

### ፫. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የመጠቀም ግዴታ

በባለስልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ዝርዝራቸው የሚወሰን ታክስ ከፋዮች በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት እውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የሽያጭ ደረሰኞችን አዘጋጅተው የማውጣት ግዴታ አለባቸው፡፡

### ፬. ደረሰኞች ሊይዟቸው የሚገቡ መረጃዎች

፩. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተዘጋጀ የሽያጭ ደረሰኝ ፡-

ሀ. በታክስ ባለስልጣኑና የንግድ ስራ ፈቃድ በሰጠዉ አካል የተመዘገበዉን የታክስ ከፋዩን ስም፣

ለ. የንግዱን ስም፣

ሐ. የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር፣

መ. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ስሪትና ሞዴል ዕውቅና ሰርቲፊኬት ቁጥር፣

ሠ.የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን የምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣

ረ. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ጥቅም ላይ የዋለበትን አድራሻ፣

application program only by using the existing interface;

## PART TWO
## USE OF SALES REGISTER MACHINES AND RECEIPT

### 3. Obligatory Use of Sales Register Machines

Taxpayers, who shall be specified in the directive to be issued by the Authority, shall be obliged to prepare and generate sales receipts in accordance with Art. 4 of this Regulation by using those Sales Register Machines that are accredited pursuant to the provisions of this Regulation hereof.

### 4. Particulars to be Incorporated in the Receipts

1. Any receipt to be prepared by the Sales Register Machine shall incorporate the folloing particulars:
   a) The name of the taxpayer registered by the Tax Authority and the body which has granted him the business license;
   b) The name of the business;
   c) The taxpayers identification number;
   d) Accreditation certificate number, brand and model of the Sales Register Machine;
   e) The registration and license number of the Sales Register Machine;
   f) The address where the Sales Register Machine is in use;

ሰ. የደረሰኙን ቁጥር፣

ሸ. ሽያጩ የተከናወነበት ቀን፣

ቀ. የተሸጠውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነትና ብዛት፣

በ. የሽያጩን ዋጋ ፣

ተ. ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ክፍያዎችን በውጭ ምንዛሬ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበል ከሆነ ክፍያውን የተቀበለበትን የውጭ ምንዛሪ ዓይነት፣ ክፍያው በክሬዲት ወይም በዴቢት ካርድ የተፈፀመ ከሆነ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርዱን ያወጣውን ኩባንያ የንግድ ስም፣

ቸ. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች መረጃዎችን ማካተት አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/በ/ መሠረት የሚጠቀሰው የሽያጭ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውንና የማይከፈልባቸውን ሽያጮች ጠቅላላ ድምር ለያይቶ ማሳየት አለበት፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሠረት በእጅ የተዘጋጀ ደረሰኝ በሚሰጥበት ጊዜ በእጅ የተዘጋጀው ደረሰኝ ቅጂ በመሳሪያው ከተዘጋጀው ደረሰኝ ጋር ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

## ፭. ስለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች አጠቃቀም

፩. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ፡-

ሀ. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሰረት

g) Number of the receipt;

h) The date in which the sale took place;

i) The type and quantity of goods or services sold;

j) The price of the sell;

k) If the taxpayer receives payments in foreign currency based on the permission granted to it by the National Bank of Ethiopia, the type of foreign currency received in cash, or if the payment has been effected by credit or debit card, the trade name of the debit or credit card-issuing company;

l) Any other information to be specified in the directive issued by the Authority.

2. The price of sell to be stated pursuant to Sub Art. 1(j) of this Article hereof, shall separately show the total taxable and non-taxable transaction values with respect to the Value Added Tax.

3. In the case of issuance of manually prepared receipt in accordance with Sub Art. /3/ of this Article hereof, the duplicate of such receipt shall be attached and preserved to the machine generated receipt.

## 5. Use of Sales Register Machines

1. A tax payer using a Sales Register Machine shall:

a) Obtain a permission that enables to use with

የሚሰጠውን በመሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ በቅድሚያ ማግኘት አለበት፡፡

ለ. መሳሪያውን ጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው በመሳሪያው ለመጠቀም በሚያስችለው ፈቃድ ላይ ለተመለከተው የንግድ ስራ ብቻ ነው፡፡

ሐ.ለባለስልጣኑ አስቀድሞ በጽሁፍ ሳያስታውቅ የንግድ ስሙን መለወጥ ወይም በመሳሪያው ላይ የጥገና፣ አቅም የማሳደግ፣ ለውጥ የማድረግ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ እንዲሆን የማድረግ ስራ ማከናወን ወይም በማናቸውም ምክንያት ከቦታው ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

መ. በመሳሪያው ላይ የጥገና፣ አቅም የማሳደግ፣ ለውጥ የማድረግ፣ የማሻሻል ወይም ወቅታዊ እንዲሆን የማድረግ ስራ ከተከናወነ በኋላ ይህንኑ ስራ ካከናወነው ሰው ጋር በመሆን የተዘጋጀ መግለጫ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፡፡

ሠ. ማናቸውንም የሂሣብ ሰነዶች የታክሱ ባለስልጣን ታክሱን ለመወሰንና ለመሰብሰብ በህግ እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስ ጠብቆ ማቆየት ይኖርበታል፡፡

ረ. መሳሪያውን በእርጅና ወይም በሽያጭ ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን ለማድረግ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ማመልከትና ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

ሰ. መሳሪያውን በመጠቀም የተከናወነውን የሽያጭ ተግባር የሚያሳይ መረጃ ለባለስልጣኑ ማስተላለፍ የሚችል

the machine issued pursuant to Art. 16 of this Regulation prior to the use of the machine;

b) Be able to use the machine exclusively only for the business purpose specified in the permission that enables him to use the machine;

c) Not beable, without prior written notice to the Authority, to change his business name or have the machine repaired, upgraded, altered, modified, updated or removed, under any circumstances, from its specified location ;

d) Following the machine's repairing, upgrading, alteration, modification or updating and prior to its re-use, submit a joint statement to the Authority prepared with the person who performed such work;

e) Preserve all accounting records for a period prescribed by law, within which the tax Authority is authorized to make assessment and collection of taxes;

f) Apply to the Authority and obtain its authorization prior to the withdrawal of the Sales Register Machine from use due to its wear and tear or sale;

g) Connect e-mobile to the Sales Register Machine which can transmit to the Authority data of sales transactions carried out using the

ተርሚናል በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ላይ መግጠም አለበት፡፡

፪. ታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ በባለስልጣኑ ፈቃድ በታተመ የሽያጭ ደረሰኝ ሊጠቀም ይችላል፡፡

፫. የሚመለከተው ባለስልጣንም፡-

ሀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ /መ/ የቀረበለትን መግለጫ መነሻ በማድረግ መሳሪያው አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት መሳሪያውን መመርመርና መገምገም አለበት፡፡

ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ /ረ/ የተጠቀሰው ማመልከቻ ሲቀርብለት መሳሪያው አገልግሎት ላይ እስከነበረበት የመጨረሻ ቀን ድረስ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች በተገቢው አኳኋን መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምርመራ ማድረግ አለበት፡፡

፬. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆን የሚሰጠው ፈቃድ መሳሪያው ከአገልግሎት ውጭ በሆነበት ቀን፡-

ሀ. የነበረውን የቆጣሪውን ንባብ፣

ለ. የተከማቸውን አጠቃላይ ሽያጭ ድምርና

ሐ. በመጨረሻ ተዘጋጅቶ የወጣውን ደረሰኝ ቁጥር ማሳየት አለበት፡፡

፭. አግባብ ያለው ባለስልጣን በደረሰኙ ራስጌ ሊሰፍር የሚገባው ፅሁፍ እስከሚዘጋጅ ድረስ ታክስ ከፋዩ ከሀያ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በሌላ

machine.

2. The taxpayer may, during the time where the Sales Register Machine is under repair, use receipts printed with the approval of the Authority.

3. The concerned Authority shall:

   a) Based on the statement submitted to it pursuant to Sub-Art. 1(d) of this Article hereof, inspect and evaluate the machine prior to its actual use;

   b) Upon receipt of the application referred to it under Sub-Art. 1(f) of this Article hereof, carry out verification inspection enabling to ensure that all sales data registered in the Sales Register machine up to the last day of its use are properly recorded.

4. The authorization for withdrawal of a Sales Register Machine from use shall indicate the following information as of the date of its withdrawal:

   a) The reading of the machine's counter;
   b) The accumulated grand total sales; and
   c) The serial number of the last receipt issued.

5. In no case shall a Sales Register Machine be used without the customer's receipt clearly indicating all the data required under the provisions of Art.

ዓይነት ደረሰኝ እንዲጠቀም ካልፈቀደ በስተቀር የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ያልያዘ ለደንበኞች የሚሰጥ ደረሰኝ ለማዘጋጀት ተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም፡፡

፮. ለደንበኞች በሚሰጠው ደረሰኝና ለኦዲት ጆርናል በሚዘጋጀው ጥቅል ወረቀት ላይ የሚሰፍረው የግብይት ቁጥር አሰጣጡ ስርዓት ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ሰርክዩት እንዲታወክ ወይም እንዲነካካ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## ፮. ስለጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም

በጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተደነገገውን ከማሟላት በተጨማሪ፡-

፩. ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ መሳሪያ ተፈላጊዎቹን ረድፎች የያዘና በተገቢው አኳኋን የተመዘገበ የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ የሽያጭ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

፪. በሁለቱም የጥቅል ወረቀቶች መጠቅለያ ወይም በተመሳሳይ አካላት ላይ የደረሰኝ ወረቀት ያልገባበት የሽያጭ ገቢ መመዝገቢያ መሳሪያ ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፡፡

፫. ለደንበኛ በሚሰጠውና በኦዲት ጆርናል ደረሰኝ ወይም በተመሳሳይ ሰነዶች ላይ የሚታተመው ፅሁፍ ሊነበብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ንዑስ የሽያጭ መዝገብ ሁልጊዜም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያው በሚገኝበት ቦታ እንዲቀመጥና

4 of this Regulation unless the appropriate Authority authorized such use, pending the completion of the installation of the official receipt header, for a period not exceeding twenty days from the date of the authorization.

6. It is prohibited to disturb or tamper the circuit of Sales Register Machine or the receipt numbering system of transaction numbers that is imprinted on the customers' receipt and the audit journal tape.

## 6. Use of Cash Register Machine

A taxpayer using the Cash Register Machine, in addition to fulfilling the requirements of Art. 5 of this Regulation, shall:

1. Maintain a sales book to register cash having the columns required for each machine used and registered properly;
2. Use a Cash Register Machine without having receipt paper in the corresponding tapes installed on both rollers or their equivalent;
3. Ensure that the imprint on the customer's and audit journal tapes, or their equivalent is legible;
4. Keep a subsidiary cash register sales book at all times at the place where the cash register machine is located, and make it available at any

ስልጣን የተሰጣቸው የባለስልጣኑ ሠራተኞች ለማመሳከር በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ እንዲያዩት ማድረግ አለበት፡፡

## ፯. ስለሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ አጠቃቀም

፩. የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያን የሚጠቀም ታክስ ከፋይ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተደነገገውን ከማሟላት በተጨማሪ እንዲጠቀምባቸው የተፈቀዱለት ሰነዶች ተከታታይ ቁጥር ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት በቀጣይ ጊዜያት የሚጠቀምባቸውን ሰነዶች ተከታታይ ቁጥር ከባለስልጣኑ ማስፈቀድ አለበት፡፡

፪. ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ የኤሌክትሮኒክ ጆርናል ሳይኖረው በስራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

፫. የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ግብይቶችን በውጭ ምንዛሬ እንዲያከናውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ከሆነ በውጭ ምንዛሬ ያከናወናቸውን ግብይቶች የሚያሳዩ መረጃዎችን በተጠየቀ ጊዜ ለባንኩ ማቅረብ አለበት፡፡

፬. ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ ፊስካል ፕሪንተር በመጠቀም ደረሰኝ ማውጣት የሚችል መሆን አለበት፡፡

## ፰. ስለኮምፒዩተር መረጃ መረብ አጠቃቀም

ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ድርጅቱ የኮምፒዩተር መረጃ መረብን የሚጠቀም ከሆነ፡-

፩. የገዛውን ሶፍትዌር ዓይነት፣ የአምራች ኩባንያውን ስም፣ የፈቃድ ሁኔታ፣ ለስንት ሽያጭ ነቁጣዎች፣ እስከመቼ የሚያገለግል መሆኑንና የማደሻውን ወቅት ማስመዝገብ አለበት፡፡

time for verification by the duly authorized officers of the Authority.

## 7. Use of the Point-of-Sale Machine

1. A taxpayer using the Point-of-Sale Machine shall, in addition to fulfilling the requirements laid down under Art. 5 of this Regulation, obtain authorization from the Authority for serial numbers to be used in the subsequent document range, at least one month before the previously authorized document range numbers are fully utilized.
2. No Point-of-Sale Machine shall be put to use with out having the corresponding electronic journal.
3. A taxpayer using the Point-of-Sale machine shall, when requested, submit reports to the National Bank of Ethiopia reports which show transactions made in foreign currency in accordance with the authorization given to him by the Bank.
4. Any Point-of-Sale Machine must be able to issue receipts by using fiscal printer.

## 8. Use of Computer Information Network

Every taxpayer, where its business firm uses a computer web site system, shall:

1. Cause the registration of the type of software purchased, the name of the manufacturing company, the licensing conditions, number of Point-of-Sale, serving duration and renewal period;

፪. ዳታ ቤዙ የሚያስተናግድበትን ሰርቨር ሞዴል፣ የሀርድ ዲስክ ቁጥርና የመረብ ካርድ ቁጥር ማስመዝገብ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት
## የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተፈላጊ ባህሪያት

### ፱. የወል ባህሪያት

ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ፡-

፩. የተመዘገበውን ቁጥር ማስተካከል በማይቻልበት አኳኋን ቢያንስ አስራ ሁለት አኃዞች የሚደርስ የተከማቸ ጠቅላላ የሽያጭ መጠንን መያዝ የሚችል፣

፪. በተመዘገበው መረጃ ላይ ለውጥ ሊደረግበት፣ ወደሌሎች አሠራሮች ሊለወጥ ወይም የሽያጭ እንቅስቃሴዎች እንዳይመዘገቡ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን ሊቀየር የማይችል፣

፫. በየዕለቱ የተከናወነውን ጠቅላላ ሽያጭና የተከማቸውን ጠቅላላ ድምር የሚያሳይ ሪፖርት ማውጣት የሚያስችል፣

፬. የማይቀያየር ማስታወሻ ያለው ወይም በውስጡ የተከማቸው መረጃ ቢጠፋ የጠፋውን መረጃ ማግኘት የሚያስችል ደጋፊ ስርዓት ያለው፣

፭. የሽያጭ ዋጋ ቅናሽ፣ ተመላሽ ሂሣብና የመሳሰሉትን የሚያሳይና አከማችቶ ሊይዝ የሚችል፣

፮. የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውንና

2. Cause the registration of the database terminal server model, hard disk number and network card numbers.

## PART THREE
## REQUIRED FEATURES OF SALES REGISTER MACHINES

### 9. Common Features

Any Sales Register Machine shall:

1. Be capable of holding, at least twelve digits, an accumulated grand total sales amount, in a condition where the recorded number cannot be adjusted;
2. Be tamper free, non-adjustable to other applications or free of other manipulations enabling to avoid the recorded data of sales transactions;
3. Enable to generate a report showing the reading of total sales transacted daily and the accumulated grand total recorded therein;
4. Have a non-volatile memory or be equipped with a recovery back-up support system while there appears to be a deletion of data accumulated therein;
5. Be capable of reflecting and storing information such as sales discount, refund and the like;
6. Enable to clearly and separately indicate sales

የማይከፈልባቸውን የሽያጭ እንቅስቃሴዎች በግልጽ ለይቶ የሚያሳይና የእነዚህኑ የተጠቃለለ አጭር መግለጫ ማውጣት የሚያስችል፣

፯. ባለስልጣኑ ታክሱን ለመወሰንና ለመሰብሰብ በህግ እስከተፈቀደለት ጊዜ ድረስ የተከማቸው መረጃ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችል፣

፰. የኢንተርኔት ማስተላለፊያ ፕሮቶኮል ሶፍትዌር ማስተናገድ የሚችል፣

፱. ለባለስልጣኑ የሽያጭ መረጃን ማስተላለፍ የሚችል የኢ-ሞባይል ቴክኖሎጂ መሳሪያ የተገጠመለት መሆን አለበት፡፡

## ፲. ስለጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጨማሪ ባህሪያት

ማናቸውም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፡-

፩. የኦዲት ጆርናል ጥቅል ወረቀት የሚይዝ መጠቅለያና ተከታታይ ቁጥር ያለው ለደንበኛው የሚሰጥ የደረሰኝ ቅጂ የሚይዝ ሁለተኛ ጥቅል ወረቀት ማሽከርከር የሚችል ወይም ተመሳሳይ አቅም ያለው፣

፪. ከሁለቱ መጠቅለያዎች አንዱ ብቻ እንዲሰራ በተደረገበት ሁኔታ መሳሪያውን ማንቀሳቀስ እንዳይቻል የሚያደርግ የመቆጣጠሪያ ስርዓት የተገጠመለት፣ እና

፫. የዋጋ ቅናሽና ተመላሽ ሂሣብ የመሳሰሉትን መረጃዎች ለደንበኛው በሚሰጠው ደረሰኝና በኦዲት ጆርናሉ ወይም ተመሳሳይ በሆነው ሰነድ ላይ ወዲያውኑ እንዲታተሙ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡

transactions that are subject to Value Added Tax and those which are non-taxable, and be capable of generating summarized short reports of same;

7. Enable to preserve the data so stored for a period prescribed by law within which the Authority is entrusted to make assessment and collection of tax;
8. Be capable of serving the software of Internet Transmission Control Protocol;
9. Be supported by e-mobile technology which can transmit sales data to the Authority.

## 10. Additional Features of Cash Register Machine

In Addition to the features described under Art. 9 of this Regulation hereof, every Cash Register Machine shall:

1. Be equipped with a roller to hold the audit journal tape and capable of holding the copy of the receipt, having consecutive number, issued for the customer and be able to roll a second roller or its equivalent;
2. Be equipped with a controlling system enabling to prevent the operation of the machine in situations where either of the rollers is made functional; and
3. Be capable of printing automatically, data such as sales discount and refund on the customer receipts tape and on the audit journal tape or on the document similar to it.

## ፲፩. ስለ ሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ ተጨማሪ ባህርያት

ማናቸውም የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ፡-

፩. የተከናወነውን ማናቸውንም የሽያጭ እንቅስቃሴ ወዲያውኑና በተሟላ ሁኔታ መሳሪያው በተገናኘበት ሰርቨር ውስጥ መመዝገብ የሚችል፣
፪. በታክስ ከፋዩ የሚቀርበውን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚሰጥ የሽያጭ ደረሰኝ ማጠቃለያን ባለስልጣኑ ከመሳሪያው በማየት ትክክለኛውን ለማመሳከር የሚያስችል፣
፫. ባለስልጣኑ የተሰረዙና የተከናወኑ ሽያጮችን ለመለየትና በታክስ ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ ሌሎች መረጃዎችን ለማየት እንዲችል የመከታተያና የማረጋገጫ ዘዴዎች ያሉት፣
፬. ታክስ ከፋዩ ግብይቶችን በውጭ ምንዛሪ እንዲያከናውን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተፈቀደለት ከሆነ በውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ የተቀበለውን የገንዘብ ዓይነት፣ ክፍያው በዴቢት ወይም በክሬዲት ካርድ የተፈፀመ ከሆነም የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርዱን ያወጣውን ኩባንያ የንግድ ስም ማሳየት የሚችል መሆን አለበት፡፡

# ክፍል አራት

# ለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ዕውቅና ስለመስጠትና ስለመመዝገብ

## 11. Additional Features of Point-of-Sale Machine

In addition to the features described under Art. 9 of this Regulation shall, every Point-of-Sale Machine shall:

1. Be capable of recording automatically and completely every sales transaction in the central server it is connected to;
2. Enable the Authority to view from the machine and verify the correct one of the sales receipt submitted by the taxpayer and issued in accordance with Art. 4 of this Regulation;
3. Have monitoring controls and verification techniques that enable the Authority to identify void and actual sales as well as other data that are not recorded in the taxpayer's books of account.
4. Be capable of showing the type of foreign currency received in cash, if the taxpayer is authorized by the National Bank of Ethiopia to undertake transactions in foreign currency, and be capable of indicating, if the payment is made by debit or credit card, the trade name of debit or credit card issuing company.

# PART FOUR

# ACCREDITATION AND REGISTRATION OF SALES REGISTER MACHINES

## ፲፪. ስለእውቅና ማመልከቻ

፩. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች አቅራቢ ማናቸውንም መሳሪያ ለሽያጭ ማቅረብ ከመጀመሩ በፊት የመሳሪያው ስሪትና ሞዴል ዕውቅና እንዲያገኝ ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ. በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተፈላጊ የሆኑትን የመሳሪያውን ባህሪያት ከሚያሳዩ ሰነዶች፣ እና

ለ. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአመልካቹን የንግድ ሁኔታ በሚመለከት ከሚጠየቁ አግባብ ካላቸው ሌሎች ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## 12. Applicationfor Accreditation

1. Any supplier of Sales Register Machines shall, prior to supplying any machine for sale, apply to the Authority for accreditation of the brand and model of the machine.
2. The application to be submitted in accordance with Sub-Art. (1) of this Article shall be submitted by attaching with:
   a) Documents attesting to the necessary features of the machine in accordance with the provisions stated under Arts. 9 through 11 of this Regulation hereof; and
   b) Other appropriate documents relating to the status of the applicants business as may be required in accordance with directives to be issued by the Authority.

## ፲፫. ስለ እውቅና ቦርድ አሰያየም፣ ተግባርና ሀላፊነት

፩. የእዉቅና ቦርዱ አባላት በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ይሰየማሉ። ተጠሪነታቸዉም ለባለስልጣኑ ይሆናል።

፪. የእዉቅና ቦርድ አደረጃጀት፣ ተግባርና ሀላፊነት የአሰራር ስርአት ዝርዝር ባለስልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

## 13. Designation, Duties and Responsibilities of the Accreditation Board

1. The members of the accreditation board shall be designated by the Director General of the Authority. They shall be responsible to the Authority.
2. The structure, duties, responsibilities and working procedures of the accreditation board shall be determined in accordance with the specific directive to be issued by the Authority.

## ፲፬. ማመልከቻዎችን ስለመመርመር

## 14. Examination of Applications

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የቀረበ ማመልከቻ ባለስልጣኑ ባቋቋመው የእውቅና ቦርድ ይመረመራል፡፡

፪. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ የተዘረዘሩትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ አመልካቹ የመሳሪያውን ፍተሻና የፕሮግራሙን ሙከራ የቦርዱ አባላት በተገኙበት ማከናወን አለበት፡፡

፫. ቦርዱ ማመልከቻውና ደጋፊ ሰነዶች ተሟልተው ከቀረቡለት ቀን አንስቶ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምርመራውን በማጠናቀቅ የውሳኔ ሀሳቡን ለሚመለከተው የባለስልጣኑ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡

## ፲፭. ስለእውቅና ሰርቲፊኬት

፩. ባለስልጣኑ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት ማሟላቱ በእውቅና ሰጭ ቦርድ ሲረጋገጥ ለመሳሪያው ስሪትና ሞዴል የእውቅና ሰርቲፊኬት ይሰጣል፡፡

፪. እውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ስሪትና ሞዴል ዝርዝር ባለስልጣኑ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ይፋ ያደርጋል፡፡

## ፲፮.እውቅናን ስለመሰረዝ

ለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስሪትና ሞዴል የተሰጠ እውቅና ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

፩. እውቅና የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በመቅረቡ ምክንያት ሆኖ ከተገኘ፤

፪. ባለስልጣኑ እንዲያውቀው ሳይደረግ

1. An application submitted pursuant to Art. 12 of this Regulation shall be examined by the accreditation board established by the Authority.
2. The applicant shall conduct inspection of the Sales Register Machine and an actual system demonstration in the presence of members of the accreditation board to attest to the fact that the machine posses the relevant features specified under Arts. 9 through 11 of this Regulation hereof.
3. The board shall submit its recommendation to the concerned officer of the Authority by completing its examination of the application and supporting documents within five working days from the date it had received same.

## 15. Certificate of Accreditation

1. The Authority shall Issue certificate of accreditation with respect to the brand and model of a Sales Register Machine where the accreditation board ascertains that the machine possesses the relevant features specified under Arts. 9 through 11 of this Regulation hereof.
2. The Authority shall officiate the list of accredited brands and models of Sales Register Machines by using various meanse.

## 16. Revocation of Accreditation

An accreditation given with respect to the brand and model of a Sales Register Machine may be revoked due to one of the following grounds where:

1. It is found that the accreditation was granted due to the presentation of false information;
2. Any modification or upgrading is made to the

በመሳሪያው ስሪትና ሞዴል ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከተደረገ፤

፫. መሳሪያው በስራ ላይ ሲውል በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፩ የተዘረዘሩትን አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ባህሪያት ሙሉ በሙሉ አሟልቶ አለመገኘቱ ሲረጋገጥ፣ ወይም

፬. የእውቅና ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፤

## ፲፯. ስለ ምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ

፩. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢ ለመሳሪያው ተጠቃሚ ሽያጭ ባከናወነ በአምስት ቀናት ውስጥ መሳሪያውን በሚመለከተው ባለስልጣን ዘንድ በተጠቃሚው ስም ማስመዝገብ አለበት፡፤

፪. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ለማስመዝገብ የሚቀርበው መረጃ ፡-

ሀ. የተጠቃሚውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ለ. የተጠቃሚውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣

ሐ. የመሳሪያውን ስሪት፣ ሞዴልና ተከታታይ ቁጥር፣

መ.የመሳሪያውን ቆጣሪ ንባብና ንባቡ የተካሄደበትን ቀን ማካተት አለበት፡፡

፫. ባለስልጣኑ ምዝገባውን እንዳከናወነ በተጠቃሚው ስም የተዘጋጀ በመሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ መሳሪያውን ላስመዘገበው አቅራቢ ይሰጣል፡፡

፬. የመሳሪያው አቅራቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት የተሰጠውን ፈቃድ ለመሳሪያው ተጠቃሚ ያስረክባል፡፡

machine's brand and model without notifying the Authority;

3. It is ascertained that the machine, during practical taste, fails to fully comply with those relevant requirements stated under Arts. 9 through 11 of this Regulation hereof; or
4. The person holding the certificate of accreditation is found to have violated the provisions of this Regulation.

## 17. Registration and Utilization Licence

1. The supplier of a Sales Register Machine shall cause the registration of the machine by the concerned Authority in the name of the user within five days from the date of selling such machine to any user.
2. The document to be submitted for the registration of a sales register machine shall include:
   a) the taxpayer's identification number of the user;
   b) the registration number of the user's for value added tax;
   c) the brand, model and serial number of the machine;
   d) The reading of the machine's counter and date when the reading was carried out.
3. The Authority shall, upon registering the machine, provide the supplier a license issued in the name of the user that enables to use the machine.
4. The supplier shall handover to the user of the machine the license issued pursuant to Sub-Art. (3) of this Article hereof.

፭. እውቅና የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በቀጥታ ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ተጠቃሚው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከቱትን መረጃዎች ለባለስልጣኑ አቅርቦ መሳሪያውን ማስመዝገብና በመሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችለውን ፈቃድ ከባለስልጣኑ መውሰድ አለበት፡፡

፮. በመሳሪያው ተጠቃሚ የሆነ ታክስ ከፋይ የተሰጠውን በመሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ደንበኞቹ ሊያዩት በሚችሉት አኳኋን በመሳሪያው ላይ መለጠፍ አለበት፡፡ ማመሳከር እንዲቻልም የመሳሪያው ተከታታይ ቁጥር ጐልቶ በሚታይ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

## ፲፰. ስለተሸጡ መሳሪያዎች ዝርዝር

፩. አቅራቢው ለተጠቃሚዎች የሸጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ዝርዝር የያዘ መግለጫ ወሩ በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቀርበው መግለጫ ስለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ፡-

ሀ. የመሳሪያውን ስሪትና ሞዴል፤

ለ. የመሳሪያውን ስሪትና ሞዴል እውቅና ሰርቲፊኬት ቁጥር፤

ሐ. የመሳሪያውን የምዝገባና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፤

መ. የተሸጠበትን ቀን፤

ሠ. የምዝገባው ቀን፤

5. Where the user directly imported the Sales Register Machine, he shall furnish the documents referred to in Sub-Art. (2) of this Article to the Authority and obtain a license enabling him to use the machine.

6. A taxpayer who uses the machine shall affix the license on the machine so that it shall be conspicuously visible to customers; the serial number of the machine should also be printed in bold figures to facilitate verification.

## 18. List of Machines Sold Out

1. The supplier of the Sales Register Machines shall submit a statement showing the list of machines sold out to the Authority within fifteen days from the end of a month.

2. The statement to be submitted pursuant to Sub-Art. (1) of this Article shall, with respect to each Sales Register Machine, contain the following information:

a) the brand and model of the machine;

b) the accreditation certificate number of the brand and model of the machine;

c) the registration and utilization license number of the machine;

d) the date of sale;

e) the date of registration;

ረ. የተጠቃሚውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

ሰ. መሳሪያው ጥቅም ላይ የሚውልበትን የንግድ ስራ ዓይነትና አድራሻ፤

ሸ. የመሳሪያውን ቆጣሪ ንባብና ንባቡ የተወሰደበት ቀን፣ እና

ቀ. የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያን በሚመለከት አገልግሎት ላይ የዋለውን ፕሮግራምና በፕሮግራሙ ላይ የተደረገውን ማስተካከያ ያካተተ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

፫. ባለስልጣኑ መግለጫው እንደደረሰው በራሱ ዘንድ ከሚገኘው የምዝገባ መረጃ ጋር ዝርዝሩን ማመሳከር አለበት፡፡

## ፲፱. የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያን ለተለያዩ የንግድ ስራዎች መጠቀምን ስለመፍቀድ

፩. ባለስልጣኑ የተለያዩ የንግድ ስራ ዓይነቶችን የሽያጭ መረጃ ማከማቸት የሚያስችል አቅም ያለው የጥሬ ገንዘብ መዝገቢያ መሳሪያ ለተለያዩ የንግድ ስራ ዓይነቶች የሽያጭ ደረሰኝ አዘጋጅቶ እንዲያወጣ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ሆኖም በተለያዩ የንግድ ስራዎች የሚከናወነው ሽያጭ መሳሪያው በሚጠቀምበት ጥቅል ወረቀት ላይ በምልክት ሳይሆን በቃላት በግልጽ ተለይቶ የሚፃፍ መሆን አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ፈቃድ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ በመሳሪያው አቅራቢ ወይም ተጠቃሚ

f) the user's taxpayer identification number and Value Added Tax registration number;

g) the type of business and the address where the machine is to be used;

h) the reading of the machine's counter and the date when the reading was taken; and

i) In case of a Point-of-Sales Machine, the program used for the service and the customization made thereon.

3. The Authority shall reconcile, following the submission of the statement, the list with its own registration database.

## 19. Authorizing the Use of Cash Register Machine for the Various Types of Business Activities

1. The Authority may permit a cash register machine having the capacity to accumulate sales data of various types of business to issue sales receipts for various types of business activities; provided, however, that the transaction undertaken on different types of businesses shall be clearly indicated on the machine tapes in words rather than in symbols.

2. The application submitted to obtaining the authorization referred to in Sub-Art. (1) of this Article shall be presented to the Authority on the part of the supplier or user of the machine.

አማካይነት ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳. ስለቅጣት

ይህንን ደንብ በመተላለፍ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሳይጠቀም የተገኘ ወይም በመሳሪያው ተጠቅሞ የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ ታክስ ከፋይ አግባብ ባለው የታክስ ሕግ በተደነገገው መሠረት በወንጀል ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

### ፳፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ታክስ ከፋዮች ይህ ደንብ ከፀና በኋላ እውቅና የተሰጣቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ከገበያ ለማግኘት በአንድ ወር የመሸጋገሪያ ጊዜ በባለስልጣኑ ዘንድ ባስመዘገቡት የሽያጭ ደረሰኝ መጠቀም አለባቸዉ፡፡

### ፳፪. ደንቡን የማሻሻል ስልጣን

የክልሉ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ይህን ደንብ የማሻሻል ስልጣን አለዉ።

### ፳፫. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ባለስልጣኑ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፳፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከጸደቀበት ከ ህዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## PART FIVE
## Miscellaneous Provisions

### 20. Penalties

A taxpayer who fails to use the Sales Register Machine or commits a fraudulent act by using such machine in violation of this Regulation shall, in addition to being held criminally responsible pursuant to the provisions of the relevant tax law, have his business license revoked.

### 21. Transitory Provision

Taxpayers shall have to use the sales receipt registered by the Authority within the transitional period of one month, after the effective date of this Regulation, to acquire the accredited Sales Register Machines from the market.

### 22. Power to Amend the Regulation

The Council of the Regional Government shall have the power to amend this Regulation.

### 23. Power to issue Directives

The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

### 24. Effective Date

This regulation shall come in to force as of December 5, 2011, on which date it has been approved by Council of the Regional Government.

ባህር ዳር
ህዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

Done at Bahir Dar
This 5th day of December,2011
Ayalew Gobezie
Head of Government
of the Amharic National Regional State